የሰ/መ/ቁጥር 116714

ቀን 20/11/2009 ዓ/ም

**ዳኞች፡**-ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡**- ናይል ኢንሹራነስ (አ/ማ) አልቀረቡም

**ተጠሪ፡**- የትግራይ ክልል ኮንስትራክሽንና መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ VC ስለማይሠራ አልቀረቡም

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

# ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች አቶ መንገሻ ክንፉ ያልከፈለውን የቫት ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሳኔ የህግና የውል መሠረት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በህንፃ ግንባታ ስራ አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የተያው በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ በሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያጣምራ የዳኝነት ስልጣን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ መንገሻ ክንፉ የምዕረብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ህንፃ ሰርቶ ለማስረከብ ከተጠሪ ጋር ያደረገው የግንባታ ስራ ውል ነው፡፡ የስራ ተቋረጭ በግንባታ ስራ ውሉን ስዋዋል የግንባታ ስራው  ጠቅላላ ዋጋ ብር 3,752,572.84 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማኒያ አራት ሳንቲም) እንደሆነ ተጠሪና የስራ ተቋራጩ በተዋዋሉት ውል ተገልጾል፡፡
2. የስራ ተቋራጩ ከተጠሪ ጋር ተዋወሎ ለሚወሰደው ቅድመ ክፍያ አመልካች የብር 636,088.08 (ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ሰማኒያ ሰምንት ብር ከዜሮ ስምንት ሳንቲም) የቅድመ ከፍያ ቦንድ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ለብር 374,169.96 (ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺ አንድ መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሳንቲም) ለሚሆን ገንዘብ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ ሰጥቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው የስር ተቋራጭ የግንባታ ስራ ውሉ መሠረት ብር 636,088.40 ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ሰማኒያ ስምንት ብር ከዜሮ አራት ሳንቲ) ቅደመ ክፍያ ከተከተጠሪ ተቀብሏል፡፡ እንዲዚሁም የስራ ተቋራጩ የተወሰነ የግንባታ ስራዎችን ሰርቶ በመጀመሪያው የክፍያ ሰርተፊኬት ብር 413,355.41  /አራት መቶ አስራ ሶስት ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከአርባ አንድ ሣንቲም) በድምሩ 1,049,443.81 /አንድ ሚሊዮን አርባ ዘጠኝ

ሺ አራት መቶ አርባ ሶስት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም) ተከፍሎታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የስራ ተቋራጭ የግንባታ ስራ ውሉን በማጓተቱና በግንባታ ስራ ውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ባለመፈፀሙ ተጠሪ የግንባታ ስራው ውሉን በማቋጥ ከሌላ የስራ ተቋራጭ ጋር የግንባታ ስራ ውል ተዋውሏል፡፡ ተጠሪ የስራ ተቋራጩ በግንባታ ስራ ውሉ መሠረት ባለመፈፀሙና ስራው ለሌላ ስራ ተቋራጭ በመስጠቱ ብር 895,294.44 ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) ተጨማሪ ወጭ የተዳርገው በመሆኑ የስራ ተቋረጩና አመልካች በሰጠው ዋስትና መጠን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

3. የስር ፍርድ ቤት በስር አንደኛ ተከሳሽና የአመልካችን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ሰጥቶ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የስር አንደኛ ተከሳሽ የሰራው የግንባታ ስራ መጠንና ዋጋ በባለሙያ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343(1) በመዝገብ ቁጥር 47229 መጋቢት 14 ቀን 2004 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በመመሪያ ከተመለሰለት በኋላ የስራ ተቋራጩ ያሰራው ስራና በግንባታ ቦታው ላይ ትቶት የሄደው የግንባታ ማቴሪያል ዋጋ ተጣርቶ እንዲቀርበለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የስራ ታቋጭ የሰራው የግንባታ ስራ ጠቅላላ ዋጋ ብር 938,738.11 /ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስምንት ሺ ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) መሆኑና የስራ ተቋራጩ በግንባታው ቦታ ላይ የተወው የግንባታ ማቴሪያልና ንብረት ግምት ብር 45,515.16 /አርባ አምስት ሺ አምስት መቶ አስራ አምስት ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም/ በድምሩ ብር 984,253.27 /ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሃያ ሰባት) ዋጋ ያለው ስራና ንብረት የስራ ተቋራጩ ለግንባታ ስራው የዋለ መሆኑ በባለሙያ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል የስራ ተቋራጩ ከአሰራው (ከተጠሪ) የወሰደው ብር 636,088.40 /ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ሰማኒያ ስምንት ብር ከአርባ ሳንቲም) የቅድመ ክፍያና ብር 344,462.84 /ሶስት መቶ አርባ አራት ሺ አራት መቶ ስልሣ ሁለት ብር ከሰማኒያ አራት ሳንቲም) በድምሩ ብር 980,551.24 /ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ሺ አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከሃያ አራት ሳንቲም) እንደሆነ በባለሙያው ተረጋግጧል፡፡ ባለሙያው ባቀረበው የሙያ ግምት መሠረት የስራ ተቋረጩ ከተጠሪ በቅድመ ክፍያነትና በመጀመሪያው የክፍያ ሰርተፊኬት የወሰደውን ብር 980,551.24 /ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ሺ አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ከሃያ አራት ሳንቲም) ሙሉ በሙሉ በግንባታ ስራው ላይ አውሎ ተጠሪ ከከፈለው ገንዘብ በተጨማሪ ብር 3,722.03 (ሶስት ሺ ሰባት

መቶ ሃያ ሁለት ብር ከዜሮ ሶስት ሳንቲም) የስራ ተቋራጩ የራሱን ገንዘብ ለግንባታ ስራ ውሉ የዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

4. የስር ፍርድ ቤት አመልካች ኃላፊ የሚሆነው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠው የስራ ተቋራጭ በግንባታ ስራ ውሉ መሠረት ለመፈፀም ባለመቻሉና ተጠሪ ከሌላ የስራ ተቋረጭ ጋር የግንባታ ስራ ውል በመዋዋሉ የደረሰበትን ተጨማሪ የግንባታ ስራ ዋጋ ብር 260,076.16 /ሁለት መቶ ስልሳ ሺ ሰባ ስድስት ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም) ላይ የስራ ተቋራጩ ያወጣው የግል ግንዘብ ብር 3,722.03 ተቀንሶ ብር 256,354.13 /ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ አራት ብር ከአስራ ሶስት ሳንቲም) አመልካች ከአንደኛ ተከሳሽ /ስራ ተቋረጩ/ ቀንሶ ገቢ ማድረግ የሚገባው ብር 140,813.72 ለምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤት ኪራይ የተከፈለ ብር 84,000ና የሁለት ዘበኞች ደመወዝ ብር 782 የዳኝነት ወጭና ኪሣራ አመልካች በስራ ተቋረጩ /አንደኛ ተከሳሽ) ጋር በአንድነትና በነጠላ ይክፈል በማለት በመዝገብ ቁጥር 47,229 ግንቦት 4 ቀን 2006 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በግቦት 4 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመቀወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍተብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር አንደኛ ተከሳሽ/ ውሉን ባለመፈፀሙ) ተጠሪ በደረሰበት ጉዳት ብር 486,949.85 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፡፡ እንደዚሁም ብር 140,813.72 የስራ ተቋራጩ ለሠራው ስራ ዋጋ ላይ ሊቀነስና ሊቻቻል ይገባ ነበር በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የስራ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለግንባታ ስራው የዋለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ለቅድመ ክፍያው ገንዘብ የመመለስ ግዴታ በውልም ሆነ ከህግ የመነጨ ግዴታ የለበትም እንደዚሁም አመልከች ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል የዋስትና ግዴታ አልሰጠም የስር ፍርድ ቤት የወሰነው አመልካች ለስራ አፈፃፀም ከሰጠው የዋስትና ገንዘብ በላይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች ለቅድመ ክፍያና ለስራ አፈፃፀም የሰጠው ዋስትና በላይ የተሰጠበት ውሳኔ የለም፡፡ ከስራ ተቋራጩ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ መሆን የሚገባው የቫት ገንዘብ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት በላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩና እንደመረመርነው የስር አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ መንገሻ ክንፈ የምእራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ህንፃ ለመገንባት የህንፃው ግንባታ ስራ ውል ከተጠሪ ጋር ስዋዋል አመልካች ሁለት አይነት የዋስትና ስነዶችን መስጠቱ ተረጋግጧል፡፡ የመጀመሪያው ተጠሪ ለስራ ተቋራጩ የሚከፈለውን ብር 636,088.48 ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ ሰማኒያ ስምንት ብር ከአርባ ስምንት ሳንቲም) አመልካች ለመሸፈን የሰጠው ቁጥሩ ኢፒቲ 0152/0708 የሆነ የቅድመ ክፍያ የዋስትና ሰነድ /Advanced payment bond) ነው፡፡

7. አሰሪው ለስራ ተቋረጩ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ የሚከፍለው የስራ ተቋራጩ ከአሠሪው በወሰደው ቅድመ ክፍያ የግንባታ ማቴሪያል የሰው ሀይልና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን በማሟላት ይግንባታ ስራውን እንዲጀምር ለማድረግና የስራ ተቋራጩ የሠራው ስራ ተለክቶ ከሚከፈለው ክፍያ ተቀናሽ እያተደረገ ለአሰሪው ተመላሽ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ አንፃር አሰሪው የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ለሥራ ተቋራጩ የሚከፈለው የስራ ተቋራጩ ከስሪው የወሰደውን የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞ የግንባታ ስራውን እንዲጀምርና እንዲሰራ ለማድረግ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ለግንባታ ስራው የሚያወለው መሆኑን ለማረጋጥና የስራ ተቋራጩ የወሰደውን የቅድመ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ለግንባታ ስራው ሳይሆን ለሌላ አገልግሎት ካዋለው ለግንባታ ስራ ያልዋለውን የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል አመልካች ከስራ ተቋራጩ ጋር በአንድነትና በነጠላ የሚከፍል መሆኑን የውል ግዴታ የገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ለወሰደው ቅድመ ክፍያ ገንዘብ የዋስትና ግዴታ የገባለት የስራ ተቋራጭ (የስር አንደኛ ተከሳሽ) ከተጠሪ ተቀብሎ የወሰደውን የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ብር 636,088.48 /ስድስት መቶ ሰላሣ ስድስት ሺህ ሰማኒያ ስምንት ብር ከአርባ ስምንት ሳንቲም) ሙሉ በሙሉ ለህንፃ ግንባታ ስራው የዋለው መሆኑንና የስራ ተቋራጩ የግንባታ ስራ በግንበታ ቦታ ላይ የተወው የግንባታ ማቴሪያልና ንብረት ዋጋ ብር 984,253.27 (ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) መሆኑንና ይህም የስራ ተቋራጩ ከተጠሪ ከወሰደው የቅድመ ክፍያ ገንዘብና የመጀመሪያ ክፍያ ብር 980,551.24 /ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር አምስት መቶ አምሳ አንድ ብር ከሃያ አራት ሳንቲም) በላይ ብር 3,722.03 /ሶስት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ሁለት ብር ከዜሮ ሶስት ሳንቲም) ከግል ገንዘብ ወጭ በማውጣት የግንባታ ስራውን የሰራ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

9. የግንባታ ስራው በመጓተቱ ምክንያት የግንባታ ስራ ውሉ በስራ ተቋራጩ ጉድለትና ጥፋት የግንባታ ስራ ውሉን ተጠሪ ያቋረጠው ቢሆንም የስራ ተቋራጩ በአመልካች ዋስትና የወሰደውን የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለህንፃ ግንባታ ስራው የዋለው መሆኑና ተጠሪ የስራ ተቋረጩ ቅድመ ክፍያ ገንዘቡን ተጠቅሞ የገነባውን የግንባታ ስራ ዋጋ ተቀናሽ በማድረግ ቀሪው የግንባታ ስራ እንዲያጠናቅቅ ከሁለተኛው የስራ ተቋራጭ ጋር የተዋዋለ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲጣራ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 136/1/ መሠረት የመደበው ባለሙያ ባቀረበው የሙያ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የስራ ተቋራጩ ከተጠሪ የወሰደው ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለግንባታ ስራው ተጠቅሞ የግንባታ ስራ የሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች የስራ ተቋራጩ ተጠሪ የሚሰጠውን ቅድመ ክፍያ ለግንባታ ስራው የሚያውለው ስለመሆኑና የስራ ተቋራጩ በሙሉ ወይም በከፍል የቅድመ ክፍያ ገንዘቡን ለግንባታ ስራው ያላዋለው እንዲሆን በሙሉ ወይም በከፊል ለተጠሪ ለመክፈል የገባው የዋስትና ግዴታ ዋናው ባለዕዳ ማለትም የስራ ተቋራጩ ከተጠሪ የወሰደውን ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለህንፃ ግንባታ ስራው የዋለው መሆኑ በመረጋገጡ ከገባው የቀድመ ክፍያ የዋስትና ግዴታ ነፃ የሚሆን መሆኑን አመልካች ከሰጠው የቅድመ ክፍያ የዋስትና ሰናድ `Advamced payment bond` መሠረታዊ ባህሪና ይዘትና ከፍተብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የንግድ ህግ ቁጥር 663(1) ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የስራ ተቋራጩ ለግንባታ ስራው ያልተጠቀመው የቅድመ ክፍያና የመጀመሪያ ክፍያ ገንዘብ የሌላ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ለስራ ተቋራጭው የከፈለው የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ያህል የግንባታ ስራ የተሰራለት መሆኑ ስለተረጋገጠ በሰጠሁት የቅድመ ክፍያ ዋስታና ሰነድ የምገደድበት ምክንያት የለም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው ነው፡፡

10. ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤት የስራ ተቋራጩ የወሰደው የቅድመ ክፍያ የሚከፈለው የስራው የህንፃ ስራ ዋጋ ክፍያ ተቀናሽ እያሆነ እንደሚሆን ተጠሪና የስራ ተቋራጩ በተዋዋሉት ውል ላይ የተገለጸ መሆን በማየትና አንድ የስራ ተቋራጭ ከአሠሪው በቅድመ ክፍያ የወሰደውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለግንባታ ስራው የዋለውና በቅድመ ክፍያነት በሌሎች ክፍያዎች የወሰደውን ገንዘብ የህል ዋጋ ያለው ወይም ከዚህ በላይ የሆነ የግንባታ ስራ የሰራ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡ ውሉ በስራ ተቋራጩ ጥፋት የተቋረጠ መሆኑ ቢረጋገጥም አመልካችም በቅድመ ክፍያ ገንዘብ ከሰጠው የዋስትና ግዴታ ነፃ ለማድረግ የሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት መሆኑን ሳያገናዘብ የሰጠው ውሳኔ አመልካች የሰጠውን የቅድመ ክፍያ ዋስትና ቦንድ /Advanced Payment/ bond` መሠረታዊ ይዘት ባህሪና አገልግሎት እንደዚሁም ከላይ የጠቀስናቸውን የፍተብሔር ህግ ቁጥር 1926 እና የንግድ ህግ ቁጥር 663(1)

ድንጋጌዎች ያላገናዘቡና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ያፈፀመውን ተመሣሣይ ስህተት መሠረት ተገቢነት ያሌላው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

11. አመልካች የቅድመ ክፍያ ዋስትና ቦንድ የሰጠለት በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው የስራ ተቋራጭ ከተጠሪ የወሰደውን የቅድመ ክፍያ ገንዘብና የመጀመሪያ ክፍያ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለህንፃው ግንባታ ስራ አውሎ ከግል ገንዘቡ ብር 3,722.53 /ሶስት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ሁለት ብር ከዜሮ ሶስት ሳንቲም) ዋጋ ያለው የግንባታ ስራ የከናወነ መሆኑ በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የስራ ተቋራጩ በቅድመ ክፍያ መልክ የወሰደው ለህንጻው ግንባታ ስራ ያለዋለ ገንዘብ የሌለበት በመሆኑ ተጠሪ አመልካችንም ሆነ የስራ ተቋራጩን በቅዲሚያ ክፍያ የወሰደውን ገንዘብ ይመልስልኝ በማለት ለመጠየቅ የሚያስችለው የህግ ወይም የውል ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የስራ ተቋራጩ ለወሰደው መጠኑ ብር 636,088.48 (ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ሰማኒያ ስምንት ብር ከአርባ ስምንት ሳንቲም) የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ከሰጠው የዋስትና ግዴታ ምንም አይነት ኃላፊነትና ተጠያቂነት የለበትም በማለት አመልካች የሰጠውን የቅድመ ክፍያ ቦንድ (Adcanced payment bond) መሠረታዊ ይዘትና ባህሪ የፍተብሔር  ህግ ቁጥር 1926 እና የንግድ ህግ ቁጥር 663 (1) መሠረት በማድረግ ወስነናል፡፡

12. የስራ ተቋራጩ በተጠሪ የወሰደውን የቅድመ ክፍያና የመጀመሪያ ክፍያ ገንዘብ በላይ የሚያወጣ የህንጻ ግንባታ ስራ መሥረቱ ተጠሪ የስራ ተቋራጩና አመልካች በቅድ መክፍያነት የከፈልኩትን ገንዘብ ይመልሱልኝ በማለት ክስ የማቅረብ መብቱን ቀሪ የሚያደርገው ብሆንም ተጠሪ የስራ ተቋራጩ በግንባታ ስራ ውሉ መሠረት ግዴታውን ባለመፈፀሙና ውሉ በስራ ተቋራጩ ጥፋት በመቋራጡ ደረሰብኝ የሚለውን ኪሣራ የስራ ተቋራጩ እንዲሸፍንና አመልካችም በሰጠው ቁጥሩ ፒ.አ.ቢ /151/ 0708 ለብር 374,269.59 (ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሁለት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ዘጠኝ ሳንቲም) በሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ መሠረት ኃላፊ ይሁንልኝ በማለት ክስ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣው አይደለም ከክርክሩ ኦዲት እንደተረዳው የግንባታ ስራ ውሉ የተቋረጠው አመልካች የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ በሰጠለት ስራ ተቋራጭ (በስር አንደኛ ተከሳሽ) ጥፋት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው የስራ ተቋራጭ አሰሪው (ተጠሪ) የግንባታ ስራ ውሉ በመቋራጡ ምክንያት የደረሰበትን ኪሳራ የመተካት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከፍተብሔር ህግ ቁጥር 1790 በፍተብሔር ህግ ቁጥር 1791ንና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት የሚቻል ሲሆን የፍተብሔር ህግ ቁጥር 3292 ንዑስ አንቀጽ 2 እና

ተከታይ ድንጋጌዎችም ተጠሪ ያቀረበውን የውሉ አለመፈፀምና በስራ ተቋራጩ ጥፋት በመቋራጡ ምክንያት የደረሰብኝ ኪሣራ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክስና ጥያቄ የሚደግፍ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. አከራካሪ የሆነው ተጠሪ ውሉ በስራ ተቋራጩ /አንደኛ ተከሳሽ/ ጥፋት ምክንያት በመቋረጡ የደረሰበትን ሁሉንም አይነት ኪሣራና ጉዳት ለስራ ተቋረጩ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠው አመልካች ከስራ ተቋራጩ በአንድነትና በነጠለ እንዲሸፍን ለመጠየቅ ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች ለቅድመ ክፍያ ገንዘብ ከሰጠው ዋስትና ነፃ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች ዋስትና በሰጠው የስራ ተቋራጭ ጥፋት ምክንያት በመቋረጡ ምክንያት የደረሰበትን ኪሣራ እንድሸፍን ለመጠየቅ የሚችለው ቁጥር ፒ.አ.ቢ 151/0708 በሆነው የመልካም ስራ አፈፃጸም ቦንድ የተገለፀውን ብር 374,269.59 /ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ድረስ ብቻ እንደሚሆን አመልካች ከሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም የዋስትና ቦንድ (performance bond) ይዘትና መሠረታዊ ባህሪና ከፍተብሔር ህግ ቁጥር 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ የግንባታ ስራ ውሉ በስራ ተቋራጩ ጥፋት በመቋረጡ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት /ኪሣራ/ መጠን ምንም ይሁን ምን የስራ ተቋራጭው እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት በፍተብሔር ህግ ቁጥር 1790 እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 3292 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነጋገ ሲሆን የስራ ውሉ በስራ ተቋራጭው ጥፋት ምክንያት በመቋረጡ ከደረሰበት ጉዳት ውስጥ አመልካችን መጠየቅ የሚችለው አመልካች በሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ቦንድ የሰጠበትን ገንዘብ የህል ማለትም እስከ ብር 374,269.59 /ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺ ሁለት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ዘጠኝ ሳንቲም) ድረስ ብቻ አንድ ከዚህ በላይ አመልካች ካሳ እንዲከፍል የመጠየቅ መብት ያሌለው መሆኑ አመልካች ከሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጎ እያለ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን የአመልካችን የኃላፊነት ጣሪያና ወሰን በማለፍ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. ከዚህ አንፃር በግንባታ ስራ ውሉ መቋረጥ ምክንያት አመልካች ከስራ ተቋረጩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ተጠሪ በክሱ የጠየቀው የጉዳት ካሣ ጥያቄ አይነትና መጠንና የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሳኔ ከላይ ከተገለፁትና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የህግ ማዕቀፎችና የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች ዋስታና የሰጠለት የስራ ተቋረጭ የግንባታ ስራ ውሉን በማጓታቱ ምክንያት ሌላ ጨረታ

አውጥቶ ስራውን ለሌላ ስራ ተቋራጭ ሲሰጥ የተያውን የዋጋ ልዩነት ብር 260,067.17 /ሁለት መቶ ስልሣ ሺ ስልሣ ሰባት ብር ከአስራ ሰባት ሳንቲም) ህንፃው ለተጠቀሚው የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወቅቱ ስራው ተጠናቅቆ አገልግሎት ባለመስጠቱ ተጠቀሚ መስራያ ቤቱ ሌላ ህንጻ ተከረይቶ አገልግሎት ለመስጠት በመገደዱ ምክንያት የተከፈለ ብር 84,000 /ሰማኒያ አራት ሺ/ የግንባታ ስራ ቦታው ለሌላ የሥራ ተቋራጭ እስከሚረከበዉ ለሁለት ዘበኞች የተከፈለዉ ደመወዝ ብር 5782/አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ብር/ እና በጋዜጣ ጥሪ ለማድረግ የወጣ ወጭ ብር 415/አራት መቶ አስራ አምስት ብር 350264.17(ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ አራት ብር ከአስራ ሰባት ሳንቲም) አመልካች በስራ ተቋራጩ ጋር በአንድነትና በነጠላ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል በማለት ያቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1790፣ የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1791፣ የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 3292 ንዑስ አንቀጽ 2ኛ ተከታይ ድንጋጌዎችን የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1922(2) እና አመልካች የሰጠዉን የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ መሰረታዊ ይዘትና ህጋዊ ዉጤት ያገናዘበ በመሆኑ ከላይ በዝርዝር የተገለፁትን የኪሳራ አይነቶችና ጠቅላላ ድምራቸዉ ብር 350264.17/ሶስት መቶ ሃምሳ ሺሁለት መቶ ስልሳ አራት ብር ከአስራ ሰባት ሳንቲም/ የጉዳት ካሳ አመልካችና እንዲከፈለዉ ተጠሪ ያቀረበዉ ጥያቄና የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከላይ መጠኑ የተገለፀዉን የኪሳራ ገንዘብ አመልካች የመክፈል ሀላፊነት እንዳለበት ገልጸዉ የሰጡት ዉሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንዳለበት ገልጸዉ የሰጡት ዉሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

15. የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከሰጡት ዉሳኔ ዉስጥ በርካታ የሕግና የፍሬ ነገር ጥያቄዎችን የማያስነሳዉ ተጠሪ ከስራ ተቋራጩ ቀንሶ ማስቀረት የነበረበትን ነገር ግን ተጠሪ ቀንሶ ያላስቀረዉን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የግብር ገንዘብ ብር 140813.27/ አንድ መቶ አርባ ሺ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም/ አመልካች የስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከሆነዉ የሥራ ተቋራጭ ጋር በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ነዉ በ2ኛ በኩል ተጠሪ በአዋ ቁር 286/1994 እንደተሻሻለዉ ለስራ ተቋራጭ ከሚከፍለዉ ክፍያ ቀንሶ የማስቀረት ሥልጣን ያለዉ ቁብወልድንግ ታክስ /ሁለት ፐርሰንት/ ነዉ ወይስ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 እንደተሻሻለ ተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብና ቀንሶ የማስቀረት ሥልጣን አለዉ? ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ገዴታ በሕግ ተጥሎበታል ወይስ አልተጣለበትም ተጠሪ ከሥራ ተቋራጩ ላገኘዉ አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ሀላፊነት አለበት ከተባለ ተጨማሪ እሴት ታክሱን የመሰብሰብ ግዴታ ያለበት የሥር አንደኛ ተከሳሽ ነዉ ወይስ ተጠሪ? ተጠሪ ተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብ ሀላፊነት አለበት ቢባል በራሱ ቸልተኝነትና

ጥፋት ላልሰበሰበዉ ተጨማሪ እሴት ታክስ አመልካች እንዲከፍለዉ ለመጠየቅ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉትን ነጥቦች በዝርዝር ማየት የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋ፡፡

16. ተጠሪ አንደኛ ተከሳሽ /የሥራ ተቋራጩ/ መክፈል የሚገባዉን ተጨማሪ ታክስ ክፍያ አመልካች ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረበዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የአዋጅ ቁጥር 255/1994 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለ ድንጋጌዎችና አመልካች ለተጠሪ ከሰጠዉ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና መሰረታዊ ባህሪና ከገባዉ የዉል ግዴታ አንፃር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነዉ መንገሻ ክንፈ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 11 የህንፃ ግንባታ የንግድ ሥራ የመስራት ፈቃድ ያለዉ ሰዉ ነዉ፡፡ የሥራ ተቋራጭ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 3 በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት መመዝብ ያለበት መሆኑ ከአመልካች ጋር የተዋዋለዉ የህንፃ ግንባታ ሥራ ዉል የተገለፀዉ የገዘብ መጠን የሚያሳይ ሲሆን የሥራ ተቋራጭ መደበኛ መኖሪያዉ ኢትዮጲያ ዉስጥ በመሆኑ ለተጠሪ በሚሰጠዉ የህንፃ ግልጋሎት ክፍያ ላይ አስራ አምስት ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ ከአመልካች ስብሰባ ለፌዴራል ገቢዎች ባለስልጣን ገቢ የማድረግ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 25 ተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

17. አመልካች የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ የሰጠለት ሰዉ መደበኛ መኖሪያዉ ኢትዮጲያ ዉስጥ በመሆኑ የሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነዉ የህንፃ ግንባታ ሥራ ሰርቶ ለሰጠዉ ግልጋሎት ከሚከፈለዉ ወይም መክፈል ከሚገባዉ የግንባታ አገልግሎት ዋጋ ላይ አስራ አምስት ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት ሲሆን የሥራ ተቋራጩ ደግሞ አመልካች ላገኘዉ የሕንፃ ግንባታ አገልግሎት ዋጋ አስራ አምስት ፐርሰንትን ከአመልካች ሰብስቦ ለግብር አስገቢዉ መሥሪያ ቤት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ የሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነዉ የሥራ ተቋራጭ ኢትዮጲያ ነዋሪ በመሆኑ ተጠሪ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባዉን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለሥራ ተቋራጭ የመክፈል እንጅ ተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብ ሥልጣን በሕግ አልተሰጠዉም፡፡ ተጠሪ ተጨማሪ እሴት ታክስ በሥራ ተቋራጩ ከሚከፈለዉ ክፍያ ቀንሶ የማስቀረትና የመሰብሰብ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 285/94/ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚኖረዉ የስ አንደኛ ተከሳሽ የሆነዉ የስራ ተቋራጩ መደበኛ መኖሪያ ኢትዮጲያ ዉስጥ ካልሆነ በሆነ ጊዜ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 285/94 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ተጠሪ በሥር አንደኛ ተከሳሽ ከሆነዉ የሥራ ተቋራጭ መሰብሰብ የነበረብኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ አመልካች ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸዉን የአዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የሕግ መሰረትና ተቀባይነት ያለዉ ክርክር ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

18. ከላይ በዝርዝር የተገለፁት ህጋዊ ምክንያቶች እንዳሉ ሆነዉ ተጠሪ በሥር አንደኛ ተከሳሽ /ለሥራ ተቋራጩ/ ክፍያ ሲፈፅም መቀነስ የሚገባኝ ነገር ግን ሳልቀነስ ክፍያ የፈፀምኩ በመሆኑ አመልካች ሊተካልኝ ይገባል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተጠሪ በሕግ የታዘዘዉንና መፈፀም የሚገባዉን ግዴታ በራሱ ቸልተኝነትና ጥፋት ሳይፈፀም መቅረቱን ገልጾ አመልካች በተጠሪ ጥፋት ላልተሰበሰበ ገንዘብ ሀላፊ እዲባልለት ያቀረበዉ ጥያቄ በፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1928 ድንጋጌዎች በማመሳሰል የህግ አተረጓገምን መርህ መሰረት አመልካችን ሊያስጠይቀዉ የማይችል በመሆኑ ጉዳዩን ያዩት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ተጠሪ ያቀረበዉን የብር 140,813.72 (የአንድ መቶ አርባ ሺ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም) አመልካች የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ ከላይ የገለፅናቸዉን የአዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋዎችና የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1928 ድንጋጌዎች ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነዉ በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 47229 ግንቦት 4 ቀን 2006ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 202764 ሚያዝያ 30 ቀን 2007ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነዉ የሥራ ተቋራጭ በቅድመ ክፍያና የመጀመሪያ ክፍያ ከተጠሪ ከወሰደዉ ብር 980,551.54(ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሺ አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከሃምሳ አራት ሳንቲም) በላይ የሆነና ዋጋዉ ብር 984,273.27(ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ሺ ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሃያ ሰባ ሳንቲም) የሆነ የህንፃ ግንባታ ስራ ያጣራና የወሰደዉን ቅድመ ክፍያ ለህንፃዉ ግንባታ ሥራ ሙሉ በሙሉ ያዋለዉ መሆኑ በመረጋገጡ አመልካች ለቅድመ ክፍያ በሰጠዉ የዋስትና ቦንድ ምክንያት በሀላፊነት የሚጠየቅበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ የሰጠዉ አንደኛ ተከሳሽ የግንባታ ሥራ ዉሉ በአግባቡ ባለመፈፀሙ የግንባታ ስራ ዉሉ በመቋረጡ ምክንያት ተጠሪ ለአዲሱ ስራ ተቋራጭ መክፈል ከሚገባዉ ገንዘብ ዉስጥ አንደኛ ተከሳሽ ከተጠሪ የሚጠይቀዉ ክፍያ ተቀናሽ ሆኖ የሚቀረዉን ብር 256,354.13 /ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ አራት ብር ከአስራ ሶስት ሳንቲም/ ተጠሪ የግንባታ ቦታዉ ለሌላ ሥራ ተቋራጭ እስከሚሰጥ ለሁለት ዘበኞች የከፈለዉን ብር 5782/ አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ብር/ ህንጻዉ ተጠርቶ ለተጠቃሚዉ አገልግሎት ባለመስጠቱ ለህንፃ ክፍያ የተከፈለ ብር 84,000 በድምሩ ብር 346,136.13/ሶስት መቶ አርባ ስድስት ሺ አንድ

መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከአስራ ሶስት ሳንቲም/ አመልካች ለተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

4. የዳኝነት ገንዘብና ሌሎች ወጭዎችን በተመለከተ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጡት ዉሳኔ መሰረት አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስነና፡፡
5. ተጠሪ የጠየቀዉን ብር 140,813.72 /አንድ መቶ አርባ ሺ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ አመልካች የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸዉ ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ